## በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን

“ከዳግም ምፅዓት በፊትና በኃላ እንዲሁም ስለ ጌታ መምጫ ቀን መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነው ትምህርት ይህ ነው።”

<u>ዳግም ምፅዓት ማለት፡</u>- ለሁለተኛ ጊዜ መምጣት ማለት ሲሆን ለሁለተኛ ጊዜ የሚመጣውም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። አስቀድሞ አዳምን ለማዳን መጥቷል ለሁለተኛ ጊዜ ደግሞ ሁሉን እንደየሥራው ለመክፈል ይመጣል። ከዳግም ምፅዓት በፊትም አስቀድመው የተናገሩ ትንቢቶች ሁሉ ይፈፀማሉ ትንቢቶቹም ብዙ ናቸው ጥቂቶቹን ግን እነሆ፣

#ጌታ ሐዋርያትን በደብረ ዘይት ሰብስቧቸው ሳለ በኋለኛው ዘመን በሚመጣው ትውልድ የሚደረገው ምልክት ምንድር ነው እስኪ ንገረን ብለው ጌታችንን ለመኑት ጌታም መለሰላቸው አላቸውም ወዳጆቼ ሆይ በኋለኛው ዘመን ለሚመጣው ክፉት ምልክት፣ ኀረታማ ኰከብ ይፈጠራል። ያን ጊዜ በያገሩ ጭንቅ ይሆናል ሹም ከሹም ንጉሥ ከንጉሥ ይጣላል። በረዶና ድንጋይ እሳትና ዲን አመድም ይዘንባል። $

ሕዝ. **38፥22** #በዚያን ጊዜ እኔ ክርስቶስ ነኝ በማለት በስሜ ይመጣሉ ብዙዎችንም ያስታሉ፤ ጦርነትም በየአህጉሩ ይነሣል ይህ ሊሆን ግድ አለውና፤ ተጠበቁ ዳሩ ግን መጨረሻው ገና ነው፤ ሕዝብ በሕዝብ ላይ መንግስት በመንግስት ላይ ይነሳል ርሃብ ቸነፈር የምድርም መናወጥ በልዩ ልዩ ሥፍራ ይሆናል እነዚህም ሁሉ የምጥ መጀመሪያ ናቸው።$

ማቴ. ***24፥4-9***፣ ማር. ***13፥4-10***፣ ሕዝ. ***38፥21***

በዚያን ጊዜ ብዙ ሰዎች ይሰነካከላሉ እርስ በርሳቸውም ለሞት አሳልፈው ይሰጣጣሉ ከአመፅና ከትዕቢት፤ ከተንኮል የተነሳ በሰዎች መካከል ፍቅር ትጠፋለች መተማመን አይኖርም አንዱም አንዱን እንደ አውሬ ይመለከተዋል።

<u>ጌታም ሲመጣ</u>

#እነሆ ከደመና ጋር ይመጣል ዓይንም ሁሉ የወጉትም ያዩታል የምድርም ወገኖች ሁሉ ስለ እርሱ ዋይ ዋይ ይላሉ።$ ራዕ. ***1÷7***

አዎን ጌታ በእልፍ አእላፋት መላዕክት ታጅቦ ሰማይና ምድር በመብረቅ እየታረሰ እሳት በፊቱ እየነደደ በታላቅ ግርማ ይመጣል። የተሰቀለበትን መስቀል ይዞ የተወጋ ጐኑን እያሳየ ደሙን እያንጠፋጠፈ በዕለተ ዓርብ ስለ እኛ ሲል የተቀበለውን መከራ እያስታወሰን ይመጣል።

ይህንን አስፈሪና ታላቅ ቀን ልበ አምላክ ዳዊት ሲገልጽ #ከክብሩ ውበት ከጽዮን እግዚአብሔር ግልጥ ሆኖ ይመጣል፤ ዝምም አይልም እሳት በፊቱ ይነዳል በዙሪያውም ብዙ አውሎ ነፋስ አለ$ መዝ. 49/50/ ፥ 2-3

#እነሆ በቶሎ እመጣለሁ ለእያንዳንዱም እንደ ሥራው መጠን እከፍል ዘንድ ዋጋዬ ከእኔ ጋር አለ$ ራዕ. 22፥12

#አዎን በቶሎ እመጣለሁ ይላል ሁሉን ቻይ አምላክ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ እንደ ቅዱስ ዮሐንስ እምነታቸውን ጠብቀው ልብሳቸውን አፅድተው ተጠናቀው ያሉት ደግሞ አሜን (ይሁንልን ይደረግልን) ጌታ ኢየሱስ ሆይ ቶሎና$ ይላሉ ራዕ. 22፥21

የሞትህ ተነሣ የሚል አዋጅ በመላዕክት አለቃ በቅዱስ ሚካኤል ይታወጃል። ሶስት ረቂቃን ነጋሪቶች አሉ። ነጋሪት ሲባል ነጋሪት እንዳይመስለን የጌታ ትዕዛዝ ነው።

#ጌታ እራሱ በትዕዛዝ በመላዕክትም አለቃ ድምፅ በእግዚአብሔርም መለኮት
ከሰማይ ይወርዳልና$1 ኛተሰ. 4፥16

- የመጀመሪያው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አውሬው የበላው ነፋስ የበተነው ያለቀው የደቀቀው ሁሉ ራሱ በፈረሰበት ቦታ ላይ ይሰበሰባል (ያዕቆብ ዘሥሩግ ቁ. 91)

- ሁለተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ አጥንትና ስጋ ተዋህደው ሳይንቀሳቀስ ትኩስ ሬሳ ይሆናል አጥንቶችና ጅማቶች ከሥጋና ከደም ጋር ይያያዛሉ እስኪነሱ ያለመንቀሳቀስ ፍፁም በድን ይሆናሉ።
- ሶስተኛው ረቂቅ ነጋሪት ሲመታ በተቃዋሚ አካል በምትናገር አንደበት ከራስ ጠጉራቸው እስከ እግር ጥፍራቸው ከቁጥር ሳይጐድሉ ከሰውነታቸው ሳይከፈሉ ወንድ በአቅመ አዳም የ 30 ዓመት ጐልማሳ ሴት በአቅመ ሔዋን የ 15 ዓመት ቆንጆ ሆነው በአርባ ቀን በእናቱ ማህፀን ደም ሆኖ የወረደ ፅንስ ሳይቀር በጐም ይሁን ክፉ ሥራቸውን ይዘው ይነሳሉ ጌታ ራሱ በማቴ. 25፥31-46 ባለው ላይ እንደጠቀሰው በጐቹን በቀኝ ፍየሎቹን በግራ ያቆማቸዋል።

<u>የክርስቶስ መምጫው ቀን ይታወቃል</u>?

#ስለዚያች ቀንና ስለ ዚያች ሰዓት ግን ከእግዚአብሔር በቀር መላዕክትም የሰው ልጅም ቢሆን አያውቁትም$ ማቴ. 24፥36 እንግዲህ ከባለቤቱ ከክርስቶስ በቀር ማንም ፍጡር አያውቃትም።

አንዳንድ የእምነት ክፍሎች ክርስቶስ ነገ ይመጣል ከነገ ወዲያ እያሉ የክርስቶስን ምፅዓት ቅርብ አድርገው ሲናገሩ ይሰማሉ ይህ እንዴት ነው?

ለዚህ ጥያቄ ቅዱስ ጳውሎስ መልስ አለው #ነገር ግን ወንድሞች ሆይ ስለ ጌታችን ስለ ኢየሱስ ክርስቶስ መምጣትና ወደ እርሱ ስለመሰባሰባችን በመንፈስ ወይም በቃል ወይም ከእኛ እንደሚመጣ በመልዕክት የጌታ ቀን ደርሶዓል ብላችሁ ከአእምሮአችሁ ቶሎ እንዳትናወጡ እንዳትደነግጡም እንለምናችኋለን፤ ማንም በማናቸውም መንገድ እያሳታችሁ ከህደቱ አስቀድሞ ሳይመጣና የአመጽ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ሳይገለጥ አይደርስምና፣ እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ አምላክ ከተባለው ሁሉ ሰዎች ከሚያመልኩት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተቃዋሚ እርሱ ነው።$

+2ኛ ተ፡2 ፥ 1 – 4

እንግዲህ አስቀድሞ ስለተነገረን ዛሬም ማንም ክርስቶስ ሊመጣ ነው እያለ ያሻውን ቢለፈልፍ ጆሮአችንን እንዳንለግሰው ተመክረናል የክርስቶስን መምጫ ጊዜ ማንም ሰው አያውቅም እርሱ ባለቤቱ ግን አስቀድሞ የሚሆነውን ሁሉ ገልጦልናል ጊዜውና ድርጊቱ ራሱ ወቅቱ መድረሱን ይገልጽልናል።

ይህ ሁሉ ይፈጸም ዘንድ ግድ ነው። ጌታ ከመምጣቱ በፊትም ጌታ ከመጣ በውኋላም ሁሉ ለሁሉ ግን ንስሐ መግባት የጌታ ሥጋና ደምን መቀበል እንደ አንድ ክርስቲያንና፣ ድህነትን ለሚፈልግ ሰው ግድ ነው።

ጌታም ሲመጣ እንዲህ ይሆናል ተብሎ እንደተፃፈ ኃጥአን ያለቅሳሉ እንባቸው እንደ ክረምት ውሃ በጉንጫቸው፣

## #ወስብሐት ለእግዚአብሔር$

እስኪሽቆለቆል። ዳሩ ግን የዚያን ጊዜ ለቅሶና እንባ ከንቱ ነው #አነሆ የማልቀሻ ወደ እግዚአብሔር የመመለሻ ወቅት ዛሬ፣ አሁን ነው።

$ ስለዚህ ከጻድቃን ጋር ለመደመር እግዚአብሔር እንደ መላዕክቱ ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ እያልን እንድናመሰግን ከአሁኑ እንዘጋጅ።

## #የመዳን ቀን ዛሬ ነው$

- የእግዚአብሔርን ትዕዛዝ ስለ ጠበቁ ስለ ፃድቃን ያን ጊዜ ከፀሐይ ሰባት እጅ አብርተው መሪያቸው ክርስቶስን መስለው ወደ ተዘጋጀላቸው መንግስት ይገባሉ።

#እግዚአብሔር እንደ ፃድቃን እንድንሆን ይርዳን$

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

ምንጭ፡-

- መጽሐፍ ቅዱስ
- አምደ ሃይማኖት
- ፍካሬ ኢየሱስ